የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶
አዲስ አበባ ሰኔ ፮ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31th Year No.50
Addis Ababa 13th June, 2022

## ማውጫ

**ደንብ ቁጥር ፻፴፪/፳፻፲፬**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ስጋት ደህንነት ደንብ**

**ገፅ……………………………………………፪ሺ፭፻፶**

## CONTENT

**Regulation Number 132/2022**
**The Addis Ababa City Government Disaster Risk Safety Regulation**

**Page…………………………………….….2550**

## ደንብ ቁጥር ፻፴፪/፳፻፲፬
## በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ስጋት ደህንነት ደንብ

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ምክንያት አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ድርጊቶችና ስጋቶች ላይ ተገቢ የሆኑ እርምጃዎችን በመውሰድ አስቀድሞ መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የከተማውን ነዋሪ ህይወትና ንብረት እንዲሁም የልማት አውታሮች ደህንነት ከማንኛውም አደጋዎች እንዲጠበቅ ማድረግ እና ማናቸውም መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማት ደህንነታቸው ተጠብቆ አስተማማኝ የሥራ አካባቢ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

## Regulation Number 132/2022
## The Addis Ababa City Government Disaster Risk Safety Regulation

**WHEREAS,** it has been found necessary to take the necessary measures on actions and risks that may cause natural and man-made disasters in Addis Ababa city to prevent the thereof before happening;

**WHEREAS,** it has been found necessary to ensure the safety of the existence and property of the residents as well as the development infrastructures of the city from any form of disaster and to create a safe working environment by ensuring the safety of any governmental, non-governmental, and private institution;

ያንዱ ዋጋ
Unit price

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

ማንኛውም የህዝብ መገልገያ ህንጻ ተቀባይነት ባለው የአደጋ ደህንነት መከላከያ መስፈርት መሰረት አደጋን ሊቋቋም እና አደጋ ቢከሰት በተጠቃሚዎችና በአካባቢው ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ሊቀንስ በሚችል መልክ ጥቅም ላይ ማዋል በማስፈለጉ፤

የአደጋ ስጋት ደህንነት መፈተሻ መሳሪያዎች አያያዝና የአደጋ ስጋት ደረጃ ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፸፬/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፺፩ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

**WHEREAS,** it has been found necessary to utilize any public service-providing building by ensuring that it employs an appropriate disaster prevention safety standard to withstand a disaster and mechanisms that minimize the injuries of customers and the damage to the area if an accident occurs;

**WHEREAS,** it has been found necessary to check the handling of disaster risk safety inspection materials and disaster risk levels;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 91 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 74/2021, the Cabinet of the Addis Ababa City Government has issued this Regulation.

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ስጋት ደህንነት ደንብ ቁጥር ፻፴፪/፪ሺ፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩. **"አዋጅ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፸፬/፪ሺ፲፬ ነው፤

፪. **"ኮሚሽን"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳትና አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ነው፤

፫. **"ተቋም"** ማለት ማንኛውም ዓይነት አምራችና አገልግሎት ሰጪ የግል፣ የመንግስት ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው፤

፬. **"አደጋ"** ማለት ታስቦበት ወይም ሳይታሰብበት ሊከሰት የሚችል በህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ ለህበረተሰቡ መደበኛ የአኗኗር ስርዓት መዛባት፣ ለኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ መቃወስ ምክንያት ሊሆን የሚችል ማንኛውም አደገኛ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ክስተት ወይም ሁኔታ ነው፤

፭. **"ከአደጋ ደህንነቱ ያልተጠበቀ ተቋም"** ማለት ለቅድመ አደጋ መከላከያና ምላሽ መስጠት የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን ያላሟላ ተቋም ነው፤

## Part One
## General Provisions

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as: "**The Addis Ababa City Government Disaster Risk Safety Regulation Number 132/2022.**"

### 2. Definition

In this Regulation, unless the context requires otherwise:

1. **"Proclamation"** means the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to specify the power and duties of the thereof Proclamation No. 74/2021;
2. **"Commission"** means the Addis Ababa City Government Fire and Disaster Risk Management Commission;
3. **"Institution"** means any kind of production and service rendering private, governmental, and non-governmental organization;
4. **"Disaster"** means any dangerous natural and man-made event or condition that may occur intentionally or unintentionally and cause damage to the lives and property of the society resulting in the disruption of the normal livelihood as well as economic, social, and environmental chaos;
5. **"Unsafe Institution"** means an institution that does not meet the requirements for pre-disaster prevention and response;

፮. **"እሳት አደጋ"** ማለት ማንኛውም እሳት ባልተፈለገ ጊዜና ወቅት በመነሳት በሰውና ንብረት ላይ ጉዳት የማድረስ ሁኔታ መኖር ነው፤

፯. **"የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር"** ማለት የአደጋ ስጋትን ለመቀነስና ለመምራት የሚያስችል የተቀናጀ ፖሊሲ፣ ስትራቴጅ፣ ዕቅድ፣ አደረጃጀት፣ አሰራር ስርዓት እና ትግበራ ነው፤

፰. **"የአደጋ ጉዳት"** ማለት በአደጋ ምክንያት የህብረተሰቡን መደበኛ የአኗኗር ሥርዓት፣ የኢኮኖሚያዊና የአካባቢያዊ ሁኔታዎችን የሚያቃውስ፣ ከፍተኛ የህይወት መጥፋትን፣ የንብረት ውድመትንና የአካል ጉዳትን የሚያስከትልና ተመልሶ ለማገገም ከተጎጂው ማህበረሰብ አቅም በላይ የሆነ ከፍተኛ ጥፋት ወይም ኪሳራ ነው፤

፱. **"የአደጋ ስጋት ቅነሳ"** ማለት የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የአደጋ መንስኤ ሊሆኑ የሚችሉ ድርጊቶችን፣ ሁኔታዎችንና ክስተቶችን በመረዳትና በመተንተን የአደጋ ስጋቶችን መቀነስ ብሎም ማስቆም ነው፤

፲. **"የአደጋ ዝግጁነት"** ማለት አግባብነት ያለው አደጋ ከመከሰቱ በፊት ለመከላከል እና ምላሽ መስጠት የሚያስችሉ ዕውቀቶችንና አቅሞችን መፍጠርና ማደራጀት ነው፤

፲፩. **"ለአደጋ ምላሽ መስጠት"** ማለት ህይወትን ለማዳን፣ የጤና ሁከት ተፅዕኖ ለመቀነስ፣ የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅና በአደጋ ወቅት ህብረተሰቡን ለመርዳት የሚሰጡ የድንገተኛ አደጋ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት መስጠት ነው፤

፲፪. **"ማካተት"** ማለት ተቋማት በልማት ዕቅዶቻቸው ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን ታሳቢ ያደረገ የማካተት ስራን በመስራት የአደጋ ደህንነታቸውን ማረጋገጥ ነው፤

6. **"Fire Accident"** means the occurrence of fire in any undesired moment and causes damage to individuals and properties;

7. **"Disaster Risk Management"** means an integrated policy, strategy, plan, organization, procedural systems, and the implementation of the thereof that enables the management and reduction of disaster risks;

8. **"Disaster Damage"** means severe harm or loss due to a disaster that disrupts the normal livelihood of the society, economic, and environmental situation and results in an immense loss of lives, property damage, and physical disabilities which will be beyond the capacity of the society to recover;

9. **"Disaster Risk Mitigation"** means the reduction or prevention of actions, circumstances, and happenings that could cause a disaster using various methods and understanding and analyzing the thereof;

10. **"Disaster Readiness"** means the establishment and organization of the relevant knowledge and capabilities that enable them to prevent and respond to a potential disaster before it happens;

11. **"Disaster Response"** means the provision of an emergency disaster prevention and controlling service to save lives, lessen the impacts of health problems, protect the safety of the society, and help the community in times of disasters;

12. **"Inclusion"** means the inclusion of disaster risk management activities and the implementation of thereof by institutions in their respective development plans to ensure safety;

፲፫. **"የጨረር አመንጪ ቁሶች አያያዝ"** ማለት የተለያዩ የጨረር አመንጭ ቁሶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋልና በተገቢው ማስወገድ ነው፤

፲፬. **"ጅምር እሳት"** ማለት ያልተስፋፋና ከፍተኛ ጉዳት ማድረስ ያልጀመረ ነገር ግን የተቀጣጠለ እሳት ነው፤

፲፭. **"የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ"** ማለት እንደ ተቀጣጣይ ነገሮች እና የእሳት ምድብ ዓይነታቸው የሚለያዩ ሆነው እሳትን ለማጥፋት የምንጠቀምባቸው የደረቅ፣ የፈሳሽና የጋዝ ውህዶችን የያዙ መሳሪያዎች ነው፤

፲፮. **"የእሳት ምድብ"** ማለት እሳትን እንደ ተቀጣጣዩ አይነትና የመቀጣጠል ባህሪ መመደብ ነው፤

፲፯. **"የህንፃ ምድብ"** ማለት የህንፃ መዋቅራዊ ውቅሮች መካከል ያለውን ርቀትና የወለሎች ብዛትን ታሳቢ ያደረገ አከፋፈል ወይም ምደባ ነው፤

፲፰. **"መሰብሰቢያ"** ማለት ለተለያዩ አገልግሎቶች የዋሉ በማንኛውም ተቋማትና ቦታ ውስጥ ፶ እና ከ ፶ በላይ ሰዎችን ሊያስተናግድ የሚችል ዝግ ወይንም ክፍት አዳራሽ ወይንም ስታዲየም ነው፤

፲፱. **"ማከማቻ"** ማለት ንብረት በዘላቂነት ወይም በጊዜያዊነት የሚከማችበት ቦታ ነው፤

፳. **"የኬሚካል ዉሁድ ዓይነት"** ማለት በጋዝ፣ በፈሳሽነትና በጠጣርነት ወይም በፓዉደር መልክ ተዘጋጅቶ በተቋማት ዉስጥ ለተለያየ ዓይነት አገልግሎት የሚዉሉ በተለያየ ዓይነት መልክ የሚዘጋጁ ንጥረ-ነገርና ኬሚካል ውሁድ ነው፤

፳፩. **"የአገልግሎት ክፍያ"** ማለት የአደጋ ደህንነት አዋጅና ደንብን ለማስፈጸም የሥልጠና፣ የቁጥጥር፣ የፍተሻና ለሌሎች ተመሳሳይ ማዕከል፣ አይሲኤስ እና መሰል ቴክኖሎጂዎችን ነው፤ የሆኑ ለአደጋ መከላከል ሥራዎች የሚከፈሉ ክፍያዎች ነዉ፤

13. **"Handling of Radiation Emission Materials"** means the proper utilization and disposal of the various types of radiation-emitting materials;

14. **"Combusted Fire"** means a fire that is burning but did not expand and cause severe damage;

15. **"Fire Extinguisher"** means the various materials that, as per the combustible equipment and the fire category, contain solid, liquid, and gaseous compounds that will be used to put out a fire;

16. **"Fire Category"** means the classification of fire according to its combustion type and nature;

17. **"Building Category"** means the classification or categorization of a building by considering the distance between the structural foundation of buildings and the number of floors;

18. **"Auditorium"** means a closed or open hall or stadium which is found in any institution or place and may be used for various services with the capacity to accommodate 50 or more individuals;

19. **"Storage"** means a place that can be used to permanently or temporarily store a property;

20. **"Chemical Compound Type"** means a substance or chemical compound that is prepared in gaseous, liquid, solid, and powder forms and used for various kinds of services in institutions;

21. **"Service Charge"** means a fee to be paid for training, regulatory, inspection, and other similar disaster prevention activities that enforce the implementation of the disaster safety Proclamation and Regulation;

፳፪. **"ቴክኖሎጂ"** ማለት በቅድመ፣ በአደጋና በድህረ አደጋ ወቅት አገልግሎት የሚሰጡ የሰፕሬሽን፣ የዲቴክሽን፣ የአላርም፣ የመረጃ

፳፫. **"ህንጻ"** ማለት ለመኖሪያ ፣ ለቢሮ፣ ለፋብሪካ፣ ለንግድ ወይንም ለማናቸውም ሌላ አገልግሎት የሚውል ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ግንባታ ነው፤

፳፬. **"ነባር ህንጻ "** ማለት ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት ግንባታው ተጠናቆ አገልግሎት የሚሰጥ ህንጻ ነው፤

፳፭. **"ግንባታ"** ማለት አዲስ ህንጻ፣ መንገድ ወይም ድልድይ መገንባት ወይም ነባር ማሻሻል ወይም አገልግሎቱን መለወጥ ነው፤

፳፮. **"ባለቤት"** ማለት ማንኛውም የህንጻ ወይም የግንባታ ህጋዊ ባለቤት ነው፤

፳፯. **"የአደጋ መንስዔና ተያያዥ አደጋዎች ተጽዕኖን ማቃለል"** ማለት የአደጋ መንስኤዎችና ተያያዥ አደጋዎች ሊያሳድሩ የሚችሉትን ተጽዕኖን መቀነስ ወይም ውስን ማድረግ ነው፤

፳፰. **"አደጋን የመቋቋም አቅም"** ማለት ለአደጋ መንስኤዎች የተጋለጠ አካል ወይም ህብረተሰብና የአሰራር ስርዓት መሠረታዊ አገልግሎቶችንና ተቋማትን የመጠበቅና ጉዳት ሲደርስባቸውም ወደነበረበት የመመለስን ጨምሮ የአደጋ መንስኤዎች ተጽዕኖዎችን የመቋቋም፣ የመከላከልና የመቆጣጠር እንዲሁም ከጉዳታቸው የማገገም ችሎታ ነው፤

፳፱. **"ኅብረተሰቡን መሠረት ያደረገ የአደጋ ክስተት ስጋት ቅነሳ"** ማለት ለአደጋ የተጋለጠ ህብረተሰብ የአደጋ ክስተት ስጋትን በመለየት፣ በመተንተን፣ ስጋቱን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ እርምጃዎችን በመውሰድ፣ የሚወሰዱ እርምጃዎችን በመከታተልና በመገምገም፣ የመቋቋም አቅማቸውን በማጎልበትና ተጋላጭነታቸውን በመቀነስ በንቃት የማሳተፍ ሂደት ነው፤

22. **"Technology"** means the suppression, detection, alarm, information center, ICS, and other similar technologies that provide service during pre-disaster, disaster, and post-disaster periods;

23. **"Building"** means a permanent or temporary construction that can be used for residential, office, factory, business, or any other purpose;

24. **"Existing Building"** means a building whose construction was completed and started to provide service before the issuance of this Regulation;

25. **"Construction"** means the construction of a new building, road, or bridge or the improvement of an existing one or changing its service;

26. **"Owner"** means the lawful owner of any building or construction;

27. **"Mitigating the Impacts of Disaster Causes and Related Disasters"** means mitigating or limiting the impacts of disaster causes and related disasters;

28. **"Disaster Resilience"** means the capacity of an organ or society or operation system that was exposed to disaster causes to protect the basic services and institutions and restore same as well as to withstand, prevent, and control the impacts of the causes of a disaster and recover from the thereof;

29. **"Community-Based Disaster Risk Reduction"** means the active participation of disaster-vulnerable society in identifying and describing the occurrences of disaster risks to prevent or reduce the risks, take measures as well as follow up and evaluate the measures taken to enhance their resilience and reduce vulnerability;

፴. **“አደጋን በይፋ ማሳወቅ”** ማለት አደጋ በደረሰበት አካባቢ የሚገኝ ጉዳዩ የሚመለከተው አካል የአደጋው ክብደት በአካባቢው አቅም በአጥጋቢ ሁኔታ መቋቋም የማይቻል እና የሌሎችን ድጋፍ የግድ የሚፈልግ መሆኑን ሲያረጋግጥ ኃላፊነት ባለው ባለሥልጣን የሚሰጥ ሕጋዊ መግለጫ ነው፤

፴፩. **“ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ስርዓት”** ማለት በአደጋ መንስኤዎችና ተያያዥ አደጋዎች ሊጠቁ ለሚችሉ ግለሰቦች፣ ቤተሰብ፣ ሕብረተሰብና ድርጅቶች ተገቢውን እርምጃ በወቅቱ በመውሰድ ሊደርስ የሚችለውን ጥፋትና ጉዳት ለመቀነስ አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ሲሆን አራት ቁልፍ ጉዳዮችን በአካባቢው ስላለው ስጋት በቂ ዕውቀት መኖር፣ ክትትል ማድረግ፣ ስለ አደጋ ስጋት ትንተና ትንበያ ማድረግ፣ ማስጠንቀቂያ ማዘጋጀትና ማሰራጨትና እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል አቅም በአካባቢ ደረጃ መኖር ናቸው፤

፴፪. **“የአደጋ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ”** ማለት እንደ ተቋማቱ ዓይነትና ሁኔታ ስታንዳርድ በተቀመጠው ደረጃ ወይንም ፐርሰንት የሚያሟሉት የብቃት ዓይነት ተረጋግጦ የሚሰጥ በየዓመቱ የሚታደስ ሰርተፊኬት ነው፤

፴፫. **“ሰው”** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

30. **“Publicizing a Disaster”** means an appropriate briefing given by the relevant authority when a local authority at the place where a disaster happened confirms the severity of the disaster and it could not be properly handled by the local community and needs the support of others;

31. **“Early Warning System”** means a system that enables undertaking the necessary preparations to reduce potential losses and injuries to those vulnerable individuals, families, communities, and organizations due to disaster causes and related disasters by taking appropriate measures promptly ; it includes four key issues; having sufficient knowledge about risks in the area, carry out supervision activities, analyze and forecast disaster risks, warning preparations and dissemination as well as creating capacity that enables to take measures;

32. **“Disaster Safety Competence Certificate”** means a certificate to be provided for institutions, as per their type and condition, through checking the kind of competency they fulfill according to an established standard or percentile, and to be renewed annually;

33. **“Person”** means any natural or juridical person.

**፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**፬. <u>የፆታ አገላለጽ</u>**

በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

**<u>ክፍል ሁለት</u>**

**<u>የአደጋ ስጋት ደህንነት መስፈርቶች</u>**

**፭. <u>መሟላት ያለባቸው የአደጋ ስጋት ደህንነት መስፈርቶች</u>**

፩. የህንጻዎችና ግንባታዎች ዲዛይን የሚከተሉትን መስፈርቶች ያሟላ መሆን አለበት፡-

ሀ) ማንኛውም ህንጻ ወይም ግንባታ በሚገኝበት ምድብ መሰረት የሚያስፈልገውን የአደጋ ስጋት ደህንነት መስፈርትን በዲዛይን ማካተት አለበት፤

ለ) ማንኛውም ህንጻ ወይም ግንባታ የሰዎችን፣ የሌሎች ግንባታዎችን እና ንብረቶችን አደጋ በሚያጋልጥ መልኩ ዲዛይን መደረግና መገንባት የለበትም፤

ሐ) በማንኛውም ህንጻ ወይም ግንባታ በስትራክቸራል ዲዛይን ውስጥ መሟላት ያለባቸው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች የእሣትና የሌሎች አደጋዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ መስፈርቶች መካተት አለበት፤

መ)የመሰረተ ልማት፣ የህንፃ ወይም የኢንዱስትሪ መዋቅር ለተጠቃሚዎቹ ምቹና አስተማማኝ የሆነ የተገልጋዩን ሁኔታና ብዛት፣ የአደጋ ተጋላጭነት፣ ይዘት ስፋት፣ ከፍታ፣ የአገልግሎት ዓይነት ከግምት ውስጥ አስገብቶ መዘጋጀት አለበት፤

**3. <u>Scope of Application</u>**

This Regulation shall be applicable within the vicinity of the Addis Ababa city government.

**4. <u>Gender Expression</u>**

In this Regulation, any expression in the masculine gender shall include the feminine.

**<u>Part Two</u>**

**<u>Disaster Risk Safety Requirements</u>**

**5. <u>Disaster Risk Safety Requirements to be Fulfilled</u>**

1. The design of buildings and constructions should meet the following requirements:

A. any building or construction must, according to its category, include the necessary disaster risk safety requirements in its design;

B. any building or construction should not be designed or constructed in a way that harms individuals, other constructions, and properties;

C. the prevention and controlling requirements for natural and man-made disasters, fire, and other disasters must be included in the structural designs of buildings or constructions;

D. the structural design of infrastructure, building, or industry should be prepared by considering its convenience and safety for customers, the condition and number of customers, disaster risks, and service type;

ሠ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተራ ፊደል (ሀ) የግንባታ ምድብ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤

፪. ማንኛውም ህንፃ እና ግንባታ በግንባታ ሂደት የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል ፡-

ሀ) ለማንኛውም ህንጻ ወይም ግንባታ ወይንም መሰረተ ልማት የግንባታ ፍቃድ ከመሰጠቱ በፊት በስትራክቸራል ዲዛይን ውስጥ መሟላት ያለባቸው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎችን የእሣት፣ የጎርፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ፣ አውሎንፋስ ፣ የመስመጥ፣ መደርመስ እና የሌሎች አደጋ መከላከያና መቋቋሚያ መስፈርቶች መካተታቸውን እና የአገሪቱን የህንጻ ስታንዳርድ ከግምት መግባቱ መረጋገጥ አለበት፤

ለ) ለእያንዳንዱ አዲስ ግንባታና ጥገና ለሚያካሂድ ሠራተኛ የአደጋ ጉዳት መከላከለያ እና የአደጋ ጥንቃቄ የግል መሳሪያዎች ሊሟላለት ይገባል፤

ሐ) በህንጻ ውስጥ ነዋሪዎች ወይም ተጠቃሚዎች እያሉ የጥገና ሥራ የሚከናወን ከሆነ ለጥገና ሥራ የሚውል ማንኛውም ቁሳ ቁስና መሳሪያ ስራ ላይ ሲውል አሠሪው አካል እና ተጠቃሚዎቹ ተገቢውን ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

E. the construction category specified under letter (A) of Sub-Article (1) of this Article shall be specified through a directive to be issued by the commission.

2. Any building or construction should fulfill the following during construction:

A. Before the issuance of a construction permit for any building or construction or infrastructure, the inclusion of disaster prevention requirements for natural and man-made disasters, fire, flood, earthquake, windstorm, drowning, landslides, and other disasters must be checked, and the building standard of the nation must be considered;

B. personal safety protection materials must be fulfilled for every employee that undertakes a new construction or maintenance work;

C. if maintenance work is carried out in the presence of residents or users in a building, the agent that undertakes the construction and users must employ the appropriate safety measures while using any construction equipment and materials.

## ፮. ስለ ህንጻ አጠቃቀም

፩. ማንኛውም አዲስ የተገነባ ህንጻ ወይም ግንባታ ወይንም መሰረተ ልማት እንደ ምድቡ የአደጋ ደህንነት መሰፈርት ሳያሟላና የአደጋ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ሳይሰጠው ህንጻውን ጥቅም ላይ ማዋል የለበትም፤

፪. ማንኛውም ነባር ህንጻ ወይም ግንባታ ጥገና ወይም የተወሰነ ለውጥ በሚደረግባቸው ጊዜ ቀደም ሲል በህንፃው መዋቅር ውስጥ የሚገኙ ማንኛውንም አደጋን ለመከላከል ብሎም ለመቆጣጠር የተገጠሙ ሲስተሞች ከዕድሳት ወይም ከጥገና በኋላ ስለመሟላታቸው ወይም ስለመተካታቸው ወይም ስለመስተካከላቸው ፍተሻ ተካሂዶና ተረጋግጦ ለህንጻው የአደጋ ደህንነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የመውሰድ ግዴታ አለበት፤

፫. በግንባታ ሂደት ላይ የሚገኝ ማንኛውም ህንጻ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ለሚያዙ ክፍሎች አጠቃላይ ግንባታ ቢጠናቀቅም አስፈላጊ የሚሆኑ የደህንነት ተግባራት መሟላታቸው እስካልተረጋገጠ ድረስ ለተጠቃሚዎች መተላለፍ የለበትም፤

፬. ማንኛውም ህንጻ ዉስጥ የሚገኙ ነዋሪዎችና ተጠቃሚዎች፣ ተከራይ ድርጅቶች እና ሌሎችም በይዞታቸው ውስጥ አደጋን አስቀድሞ ለመከላከልም ሆነ አደጋ ቢከሰት የከፋ ጉዳት እንዳያስከትል የእሳት ቃጠሎንና ሌላ ድንገተኛ አደጋን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችሉ የደህንነት መስፈርቶችን ማሟላት እና ጥንቃቄዎችን ማድረግ አለባቸው፤

## 6. About Building Utilization

1. Any new building or construction or infrastructure should not be open for service without fulfilling the requirements for disaster safety and obtaining a disaster safety competence certificate;
2. The systems that were installed in an existing building or construction to prevent or control a disaster should be inspected and checked first that it is fulfilled or replaced or repaired before the issuance of a disaster safety competence certificate when maintenance or slight modification work is undertaken for any existing building or construction;
3. Any building which is under construction should not be transferred for users until the fulfillment of the necessary safety activities is checked and confirmed even if the general construction work for the rooms, to be partially or fully occupied, is completed;
4. Residents, lessee organizations, and others that exist in any building should fulfill safety requirements that help to prevent a disaster within their landholding in advance and severe injuries if it happened as well as prevent and control fire and other accidents and take the necessary cautionary measures;

፭. የአደጋ ደህንነት መስፈረቶችን ያላሟላ ነባር ህንፃ ባለቤት የሆነ ሰው መስፈርቶችን ለማሟላት የሚጠበቅበትን የማድረግ ግዴታ አለበት፤
፮. ማንኛውም የህንፃ ባለቤት የውሃ መቅጃ ሀይድራንት የግንባታው አካል አድርጎ ከግቢ ውስጥ ማስተከል አለባቸው፤ የሚተከለው ሀይድራንት ከአደጋ ምላሽ ሰጪ ተቋም ስታንዳርድ ጋር መጣጣም አለበት፤
፯. ማንኛውም የጅምር ህንጻ ተጠቃሚ ከሚመለከተው አካል የመጠቀሚያ ፍቃድ መያዝ ይኖርበታል፡፡

**፯. ስለአደገኛ ንጥረ ነገሮች የአደጋ ደህንነት**

፩. አደገኛ ንጥረ ነገር የሚያከማቹ፣ የሚያጓጉዙ ወይም የሚጠቀሙ አካላት የአደጋ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ሊኖራቸው ይገባል፤
፪. አደገኛ ንጥረ ነገሮችን እና ጨረር አመንጪ ቁሶችን የሚያከማቹ፣ የሚያጓጉዙ ወይም የሚጠቀሙ ግለሰቦች ወይንም ተቋማት የአደጋ ደህንነት ጥንቃቄዎችን የማድረግ ግዴታ አለባቸው፤
፫. ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገርና በመቀናጀት ለአደጋ የሚያጋልጡ የተከማቹ አደገኛ ንጥረ ነገሮች እንዲወገድ ያደርጋል፡፡

**፰. ስለአደጋ መቆጣጠሪያ መሰረተ ልማቶች አያያዝና አጠቃቀም**

ማንኛውም ተቋም፡-

፩. የማዕድን ማውጣትና መቆፈር፣ የቤተ ሙከራ ግብዓቶችና ሪኤጀንቶች፣ የግብርና ግብዓቶችና ኬሚካሎች፣ የነዳጅ፣ የሀይል ማስተላለፍና አልኮል ክምችትና ስርጭት፣

5. An individual who is the owner of an existing building that did not fulfill the disaster safety requirements shall have the obligation to carry out the expected things to do so;
6. Any owner of a building should place a hydrant within its premises as part of the construction; the hydrant should meet the standard of the disaster response providing institution;
7. Any user of an uncompleted building should obtain a utilization permit from the relevant organ.

**7. Disaster Safety for Dangerous Substances**

1. Any organ that store, transport, or use dangerous substances must get a disaster safety qualification certificate;
2. Individuals or institutions that store, transport, or use dangerous substances or equipment that emit radiation are obliged to take disaster safety cautions;
3. The commission in consultation and collaboration with the relevant organs shall cause the disposal of accumulated dangerous substances that will cause a disaster.

**8. Handling and Utilization of Disaster Preventing Infrastructures**

Any institution:-

1. should check the handling and disaster risk of equipment related to mining activities, laboratory inputs and reagents, agricultural inputs and chemicals, storage and distribution of fuel, power transmission and alcohol,

የኢንዱስትሪ ግብዓቶች፣ ኬሚካሎችና የሚወገዱ ቆሻሻዎች አያያዝና አጠቃቀም፣ የትራንስፖርት አካላት፣ የህክምና ግብዓቶችና ጨረር አመንጪ ቁሶች፣ የጦር መሳሪያና ግብዓቶች እንዲሁም የደህንነት መፈተሻ መሳሪያዎች አያያዝና የአደጋ ስጋታቸው ማረጋገጥ አለበት፤

፪. እሳትን ሊቋቋሙ የሚችሉ ግብዓቶች፣ ዕቃዎች፣ አውቶማቲክና ማንዋል የአደጋ መከላከያና መቆጣጠሪያ ስርዓት ሊኖረው ይገባል፤

፫. ከካርቦን ሞኖ ኦክሳይድና ሰልፈር ዳይኦክሳይድ፣ ወይንም ተመሳሳይ ኬሚካሎች ነጻ መሆን አለበት፤

፬. አደጋን ሊያስከትሉ የሚችሉ ግብዓቶች፣ ምርቶች እና ጥሬ ዕቃዎች አያያዝ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ ከአደጋ ስጋት አንጻር በሚቀመጡ መስፈርቶች መሰረት መሆን አለበት፤

፭. በህንጻ ላይ የሚገጠሙና ጥቅም ላይ የሚውሉ ማናቸውም መሳሪያዎች፣ ዕቃዎች እና ግብዓቶች ከአደጋ ስጋት አንጻር የሚያስከትሉት ችግር እና እሳትን የመቋቋም ሁኔታቸው መለየት አለበት፤

፮. ማንኛውም ግንባታ፣ መሰረት ልማት ወይም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምና አያያዝ ከህብረተሰቡ አኗኗር፣ ባህል፣ እና እሴቶች ጋር የተናበበ እና ከአደጋ ስጋት ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤

፯. እንደ ተቋማቸው ሁኔታ የአደጋ መሰረተ ልማቶችን ለመጠቀም የሚችል የሰለጠነ የአደጋ ደህንነት ባለሙያ ሊኖራቸው ይገባል፤

፰. ማንኛውም ተቋም ወይንም ግለሰብ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ስጋትና ተጋላጭነት ለመቀነስ፣ ለመከላከል፣ የአደጋ መንስኤና ተያያዝ ተፅኖዎችን ለማቅለል፣

industry inputs, management and utilization of chemicals and disposable materials, transportation entities, medical inputs and radiation emitting materials, weapons, and its inputs as well as security equipment;

2. should have fireproof inputs and materials as well as automatic and manual disaster prevention and controlling system;
3. should be free from carbon monoxide and sulfur dioxide or other similar chemicals;
4. the handling, utilization, and disposal of inputs, products, and raw materials that could cause a disaster must be as per the determined requirement regarding disaster risks;
5. the anticipated problems and fire resistance conditions of any material, equipment, and inputs that will be installed and used in buildings should be identified concerning disaster risks;
6. the utilization and handling of any construction, infrastructure, or natural resource should be checked that it conforms with the livelihood, culture, and values of the society and free from disaster risks;
7. should have a trained disaster safety professional that can use disaster infrastructures as per the context of their institutions;
8. any institution or individual should strive to enhance its ability to reduce and protect natural and man-made disaster risks and vulnerability, minimize disaster causes and related impacts,

የአደጋ መቋቋም አቅም ለመፍጠር እና የአደጋ ደህንነት ባህሉን ለማሳደግ መስራት ይኖርበታል፤

፱. ማንኛውም ተቋምም ሆነ ግለሰብ በሚሰራው መሰረተ ልማት ሆነ የተለያየ ግንባታ ሥራ ምክንያት የሚከመር አፈርና የግንባታ ተረፈ ምርት፣ የተቆፈረ ጉድጓድ፣ ያልተከደነ የፍሳሽ መስመር እና ሌሎች ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ ያልተጠናቀቁ የግንባታ ስራዎች ሰዎችን ለአደጋ የማያጋልጥ መሆኑን የማረጋገጥና የመከላከያ ሥራዎችን የመስራት ኃላፊነት አለበት፤

፲. ማንኛውም ተቋምም ሆነ ግለሰብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፱) የተገለጸው ጥንቃቄ ባለማደረጉ ምክንያት ለሚደረስ አደጋና ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል ፡፡

## ፱. በአሰራር ሂደቶች መደረግ ስለሚገባቸው የአደጋ ስጋት ደህንነት ጥንቃቄዎች

ማንኛውም ተቋም በማምረት፣ በማከማቸት፣ በመጠቀም፣ በማሰራጨት ወይም በማስወገድ የአሰራር ሂደቶች የሚከሰቱ አደጋዎችን ለመከላከል የአደጋ ስጋት ደህንነት ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡

create disaster resilience capacity and a culture of disaster safety;

9. any institution or individual should have the responsibility to check that the dumped soil and construction by-products, excavated wells, uncovered sewerage lines, and other uncompleted construction works that could cause a disaster are not harming the people and undertake prevention activities;

10. any institution or individual shall be held accountable for a disaster and injuries that will be caused due to not employing the cautions specified under Sub-Article (9) of this Article.

## 9. Disaster Risk Safety Precautions that should be considered during Operation Process

Any institution should implement disaster risk safety precautions to prevent potential disasters in the production, storage, utilization, distribution, or disposal process.

## ክፍል ሦስት

## የባለድርሻ አካላትን ተግባርና ኃላፊነት ስለመወሰን

### ፲. የኮሚሽኑ ተግባርና ኃላፊነት

በአዋጁ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ሲባል ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. በማንኛውም የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አደጋ በተከሰተበት ቦታ በመግባት አደጋን ይቆጣጠራል፤

፪. ለአደጋ ስጋት ደህንነት ሙያ ምክር ይሰጣል፤ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፤

፫. በአደጋ ስጋት ደህንነት ሙያ ምክር፣ ቴክኒክ ድጋፍ ፣ ፍተሻና ብቃት ማረጋገጥ በተመለከተ ከአዲስ አበባ ከተማ ክልል ውጪ ሲጠየቅ ድጋፍ ያደርጋል፤

፬. ለአደጋ ደህንነት ስጋት የሆኑትን ቦታዎች፣ መሰረተ ልማቶች፣ ተቋማት፣ መንገዶች፣ የነዳጅ ማከማቻዎች፣ ኢንዱስትሪ ወይም መጋዘኖች እንደ አደጋ ሁኔታ ለጊዜው ይከለክላል፤ ያዘጋል፤ ከፀጥታ ሀይሉ ጋር በቅንጅትና በትብብር ይሰራል፤

፭. ለአደጋ ምላሽ ወቅት የተቋሙን የአደጋ ማሽነሪ፣ አምቡላንስና ባለሙያ ይዞ በመገኘት ለአደጋ ምላሽ ይሰጣል፤

፮. ከአደጋ ስጋት ደህንነት ጋር የተያያዙ ግዴታዎችን ባልተወጡ አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፤

## Part Three

## Determining Duties and Responsibilities of Stakeholders

### 10. Duties and Responsibilities of the Commission

Without prejudice to the power and duties specified under the Proclamation, the commission shall have the following specific duties and responsibilities:

1. avail itself at the scene of a disaster without any precondition and control thereof during any fire and emergency accidents;
2. provide advice on disaster risk safety profession; give technical support;
3. provide support regarding advice, technical support, inspection, and competency assurance on disaster risk safety profession upon the request of regions outside the city of Addis Ababa;
4. temporarily prohibit and close places, infrastructures, institutions, roads, fuel depots, industries, or warehouses that are potential risks of a disaster; work in collaboration and coordination with the security forces;
5. use the machinery, ambulances, and professionals of the institution and give response for a disaster;
6. take administrative measures on those institutions that fail to fulfill their obligations regarding disaster risk safety; cause the taking of legal measures;

፯. በከተማዋ የጅምር እሳት መከላከያና መቆጣጠርያ መሳሪያዎችን አገጣጣም፣ አተካከል፣ አጠቃቀም፣ አያያዝ፣ የመቆጣጠር፣ የማረጋገጥ ሥራ ይሰራል ወይም ስልጠና ይሰጣል፤

፰. የአደጋ ስጋት ደህንነት ፍተሻ በመደበኛነት ወይንም በድንገት አሳውቆ ያደርጋል፤

፱. ማንኛውም ተቋም፣ ህንጻ ወይም የልማት አውታር የመጠቀሚያ ፍቃድ ከማግኘቱ በፊት የአደጋ ስጋት ደህንነት ብቃት ያረጋግጣል፤ መስፈርቱን ሲያሟላ የአደጋ ስጋት ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤

፲. የአደጋ ደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ደረጃዎችን የሚወስኑ ስታንዳርዶችን፣ ኮድና የአፈጻጸም መመሪያዎችን ያወጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ፲፩. ስለተቋም ኃላፊነት

፩. በየጊዜው ለተቋሙ የሚሰጣቸውን የአደጋ ስጋት ደህንነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን፣ የሙያና የቴክኒክ ድጋፎችንና ግብረ-መልሶችን ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ፤

፪. የተቋሙንና የአካባቢውን ህልውና፣ ንብረትና ደህንነት ለመጠበቅ አደጋ ከመከሰቱ በፊት አስቀድሞ የአደጋ ደህንነት መስፈርቶችን ማሟላትና የጥንቃቄ ህጎችን በማክበር ተግባራዊ ማድረግ፤

፫. በተቋሙ ውስጥ እንደ ድርጅቱ የሥራ ባህሪይ ለአደጋ መከላከልና መቆጣጠር ሥራ የሚያገለግሉ የእሳት ማጥፊያ እና የግል ጉዳት መከላከያ መሳሪያዎችና መስፈርቶች እንዲሟሉ ማድረግ፤

፬. ተቋሙን በተወሰነ ጊዜ በማስፈተሽ ደህንነቱ እንዲረጋገጥ ማድረግ፤

7. provide training on the assembly, institution, utilization, handling, controlling, and verification of materials to be used for the prevention and controlling of combusted fire in the city;
8. undertake regular disaster risk safety inspections or carry out same by notifying it instantly;
9. any institution, building, or infrastructure should conform to its qualification for disaster risk safety before obtaining a utilization permit; a disaster risk safety competency certificate shall be provided upon meeting the requirements;
10. issue standards, codes, and implementation directives that determine the levels of disaster safety competency verifications.

## 11. Responsibility of an Institution

1. Take awareness creation training, professional and technical supports, and feedbacks that are often given to the institution regarding disaster risk safety;
2. Fulfill disaster safety criteria in advance and implement cautionary measures before the occurrence of a disaster to protect the existence, property, and safety of an institution and its surrounding;
3. Ensure the availability of fire extinguishers and personal injury protection equipment and fulfill requirements that are necessary for the prevention and controlling of a disaster in the institution as per the nature of the thereof;
4. Inspect the institution seldom to ensure the safety of the thereof;

፭. በተቋሙ ውስጥ አደጋን በብቃት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተሟላ ዝግጅትና አቅም ለመፍጠር ከኮሚሽኑ ጋር ወይም በራሱ አቅም በየጊዜው የተቀናጀ ልምምድ ማከናወን፤

፮. በተቋሙ ስትራቴጂክ የልማት ዕቅዶች ውስጥ የአደጋ ስራ አመራር ስራ ማካተት፤

፯. በተቋሙ ውስጥ የሚያስፈልጉ ማንኛውም የአደጋ ደህንነት መስፈርቶችን በማሟላት የደህንነት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፤

፰. ተቋሙ የሰለጠነ እና የብቃት ማረጋገጫ ያለው የአደጋ ደህንነት ባለሙያ በመቅጠር የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ ዝግጁነትና ምላሽ አቅሙን ማረጋገጥ አለበት፤

፱. በተቋማቱ ውስጥ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ክበብ ወይም የአደጋ ደህንነት ኮሚቴ የአደጋ ደህንነት ስራ ክፍል ወይም ባለሙያ እንደ ተቋማቱ ሁኔታ በማቋቋም የአደጋ ደህንነት እንዲጠበቅ ማድረግ አለበት፡፡

፲፪. <u>**የእሳትና ድንገተኛ አደጋዎች መከላከያና መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች አቅራቢ ኃላፊነት**</u>

ማንኛውም የአደጋ መከላከያ እና መቆጣጠሪያ እቃዎች አቅራቢ ከውጭ ሀገር እቃዎች በማስገባት ወይም ከአስመጪዎች በመቀበል የሚሸጥ፣ የሚያከፋፍል፣ የሚሞላ፣ የሚጠግን፣ እና የሚፈትሽ አቅራቢ፡-

፩. ጥራታቸውና ደህንነታቸው የተጠበቁ አገልግሎቶችን መስጠት፤

፪. ለተሰማራበት የሥራ ዘርፍ ዕውቅናና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የማውጣትና በየዓመቱ ማሳደስ፤

5. Carry out integrated practices by itself or jointly with the commission regularly to create complete readiness and capacity that enables to effectively prevent and control of an accident in the institution;
6. Incorporate disaster risk management activities in the strategic development plans of the institutions;
7. Fulfill all the necessary disaster safety requirements in the institution and possess a safety competence certificate;
8. The institution should hire a trained and certified disaster safety professional and ensure its disaster mitigation, readiness, and response capacity.
9. Establish disaster risk mitigation club or disaster safety committee or disaster safety department or has a disaster safety expert in an institution and ensure disaster safety in the thereof.

12. <u>**Responsibilities of Suppliers of Fire and Emergency Disasters Prevention and Controlling Equipment**</u>

Any supplier of disaster prevention and control materials or any individual that sells, distributes, fills, repairs, and inspects such materials by importing or receiving them from suppliers should:

1. provide quality and safe service;
2. have a permission and competency assurance certificate in the business and renew it annually;

## ክፍል አራት

## ስለ ቦርድ መቋቋም፣ ተግባርና ኃላፊነት

**፲፫. የቦርድ መቋቋም**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአደጋ ስጋት ደህንነት ደንብን የሚያስፈጽሙ የመንግሥት አስፈጻሚ ተቋማትን የሚያቀናጅ የሥራ አመራር ቦርድ /ከዚህ በኃላ "ቦርድ" እየተባለ የሚጠራ/ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**፲፬. የቦርዱ አባላት አሰያየም**

፩. የቦርዱ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና አባላት በከንቲባው ይሰየማል፤

፪. የቦርዱ ተጠሪነት ለከንቲባው ይሆናል፤

፫. የቦርዱ አባላት በሙያና በሥራ ቅንጅት አግባብነት ካላቸው የመንግሥት ተቋማት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ወይም መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት የተውጣጡ ይሆናሉ፤

፬. ማንኛውም የቦርድ አባል በማንኛውም ምክንያት የቦርድ አባልነቱን የተወ እንደሆነ ሌላ ተተኪ አባል በከንቲባው ይሰየማል፤

፭. የቦርዱን ቃለ-ጉባኤ በአግባቡ ለመያዝ፣ የቦርዱን ውሳኔዎችና ሰነዶች በሚገባ አደራጅቶ ለመያዝ ብቃትና ችሎታ ያለው አንድ ሠራተኛ በፀሐፊነት በኮሚሽኑ ይመደባል፡፡

**፲፭. የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት**

፩. ለዚህ ደንብ አፈጻጸምና የደንቡን ዓላማ ለማሳካት በአደጋ ስጋት ደህንነት ሥራ ላይ ግንኙነት ያላቸውን ተቋማት ያቀናጃል፤ ያስተባብራል፤

፪. የአደጋ ስጋት ደህንነት ስራ ቅንጅት፣ ቁጥጥርና አቅም ግንባታን በሚመለከቱ ሙያዊና ቴክኒካዊ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤

## Part Four
## Establishment of the Board, its Duties, and Responsibilities

**13. Establishment of the Board**

A management board that integrates the executive organs of the government which implement the Addis Ababa city government disaster risk safety Regulation (hereinafter referred to as the **"Board"**) is hereby established by this Regulation.

**14. Assigning of Board Members**

1. The chairperson, deputy chairperson, and members of the board shall be assigned by the mayor;
2. The board shall be accountable to the mayor;
3. The board members shall, in terms of profession and working relations, be taken from the relevant public institutions, and as deemed necessary, from various segments of the society or non-governmental organizations;
4. If any member of the board resigns from his membership due to any reason, another member shall be assigned by the mayor as a replacement;
5. The commission shall assign a competent employee as a secretary to properly organize and maintain the minutes, decisions, and documents of the board.

**15. Duties and Responsibilities of the Board**

1. Integrate and coordinate institutions that have relations in the activities of disaster risk safety for the implementation of this Regulation and the attainment of its objectives;
2. Consult on professional and technical matters concerning the integration, controlling, and capacity building of disaster risk safety activities;

አስፈጻሚ ተቋማት በቅንጅት እንዲሰሩ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

፫. በሰዎች ህይወትና ንብረት ሊከሰት የሚችልን ማንኛውም ድንገተኛ አደጋ ታሳቢ በማድረግ ወይም ስጋት አለ ተብሎ በተለዩ አካባቢዎች በሚገኙ ተቋማትና የልማት አውታሮች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሚመለከታቸውን ተቋማት በማቀናጀት የአደጋ ዝግጁነት እና የአደጋ ስጋት ቅነሳ ተግባራት እንዲከናወኑ ያድርጋል፤

፬. በቅንጅት የተሠሩ ሥራዎችን ይገመግማል፣ በሥራ ሂደት ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ይመክራል፣ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፤

፭. የቦርዱን ውሳኔዎች ለተቀናጁ አስፈጻሚ አካላት ተግባራዊ እንዲያደረጉ ይመራል፣ ይከታተላል፤

፮. በአደጋ ስጋት ደህንነት ጋር በተያያዙ የጋራ ተግባራት ላይ ግዴታቸውን ያልተወጡ የተቀናጅ አስፈጻሚ ተቋማት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ያሳስባል፤

፯. በቅንጅት አሰራሩ ውስጥ ባለድርሻ አካላቱ ባልተግባቡባቸው ጉደዮች እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት ግዴታቸውን ባልተወጡ አስፈጻሚ ተቋማት ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ የውሳኔ ሀሳብ ለከንቲባው ያቀርባል፤

፰. ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ከከንቲባው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

set directions for executive organs to work in collaboration; follow up the performance of the thereof;

3. Coordinate the concerned institutions to carry out disaster readiness and disaster risk mitigation activities through anticipating any emergency disasters that could happen to the lives and properties of the people or to prevent damages to institutions and infrastructures that are found in identified disaster threat areas;
4. Evaluate activities that were carried out in a coordinated manner; deliberate on problems faced during the process; set directions for solutions; follow up the implementation of the thereof;
5. Deliver the decisions of the board to the integrated executive organs to implement the thereof; follow up on same;
6. Urge those integrated executive organs that fail to meet their obligations regarding their common activities to carry out their respective responsibilities concerning disaster risk safety;
7. Submit a decision proposal to the mayor on matters of the integrated procedure that the stakeholder have differences and for the taking of remedial measures on the executive organs that failed to meet their obligations as per Sub-Article (6) of this Article;
8. Carry out other activities delegated by the mayor for the implementation of this Regulation.

## ፲፮. የቦርዱ ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

የቦርዱ ሰብሳቢ፦

፩. ቦርዱን በሰብሳቢነት ይመራል፤ የስብሰባ ጥሪ እንዲተላለፍ ያደርጋል፤ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረግ ግንኙነት ቦርዱን ይወክላል፤

፪. የቦርዱ ስብሰባ ወቅቱን ጠብቆ እንዲካሄድ ያደርጋል፤ አስቸኳይ ስብሰባ መጥራት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጥሪው ለቦርድ አባላቱ እንዲተላለፍ ያደርጋል፡፡

፫. የቦርዱ ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

፬. የቦርዱ ውሳኔዎችና ሰነዶች በቦርዱ ፀሀፊ አማካኝነት በሚገባ ተደራጅተው መያዛቸውን ይከታተላል፡፡

## ፲፯. የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ኃላፊነት

፩. የቦርዱ ሰብሳቢ በማይኖርበት ወቅት ተክቶት ይሰራል፤

፪. በቦርድ ሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## ፲፰. የቦርዱ ስብሰባ ሥነ-ሥርዐት

፩. የቦርዱ ስብሰባ ምልዐተ-ጉባኤ የሚኖረው ከአባሎቹ ከግማሽ በላይ በስብሰባው ሲገኙ ነው፤

፪. የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በወር አንድ ጊዜ ይደረጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ሲጠራ ቦርዱ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፤ የቦርዱ ውሳኔ በሙሉ ድምጽ ወይም በአብላጫ ድምጽ ይተላለፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል በተከፈለ ጊዜ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤

፫. የቦርዱ ፀሀፊ በየስብሰባው በተገኙ አባላት የሚፈረም ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤

## 16. Duties and Responsibilities of the Chairperson of the Board

The chairperson of the board shall:

1. presides over the board; calls for meetings; represents the board in its dealing with third parties;
2. holds the meeting of the board regularly; if he finds the calling of an extraordinary meeting is necessary, notify same to the board members;
3. ensures the implementation of the decisions of the board;
4. follow up that the decisions and documents of the board are properly organized and maintained by the secretary of the board.

## 17. Duties and Responsibilities of the Deputy Chairperson of the Board

1. Act on behalf of the chairperson in his absence;
2. Carry out other activities given by the chairperson of the board.

## 18. Meeting procedure of the Board

1. There shall be a quorum where more than half of the members of the board are present at a meeting;
2. The ordinary meeting of the board shall be held once a month; however, the board may hold an extraordinary meeting at any time as may be found necessary upon the request of the chairperson; the decisions of the board shall be passed unanimously or by majority vote; however, in case of a tie, the chairperson shall have a casting vote;
3. The secretary of the board shall record a minute that will be signed by members that are present at a meeting;

፬. ቦርዱ የሚመክርባቸውን ጉዳዮች ይህን ደንብ ለማስፈጸም የዚህ ቦርድ አባላት የሆኑ የአስፈጻሚ ተቋማት ኃላፊዎች የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡

፭. ከስብሰባው ሶስት ቀናት በፊት የቦርዱ ስብሰባ አጀንዳ ለአባላት መድረስ አለበት፤

፮. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የውስጥ የስብሰባ እና አሰራር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## የተከለከሉ ድርጊቶች፣ እርምጃ አወሳሰድና አስተዳደራዊ ቅጣት

### ፲፱. ስለተከለከሉ ድርጊቶች

፩. በማንኛውም መተላለፊያ መንገድ ላይ የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ ተሽከርካሪዎችንና መሳሪያዎችን በቀላሉ መተላለፍ እንዳይችሉ የሚያግዱ ተግባራትን መፈፀም፤

፪. ማንኛውም የአደጋ መከላከል እና መቆጣጠር ተግባራት ላይ የተሰማራን የኮሚሽኑ ሠራተኞች ሥራቸውን በአግባቡ እንዳያከናውኑ ጣልቃ መግባት፣ ማወክ ወይም ማገድ፤

፫. በሲኒማ ቤቶች፣ ቲያትር ቤቶች፣ ስታዲየሞች ወይም ሌሎች የህዝብ መሰብሰቢያ ህንፃዎች ውስጥ ከተፈቀደው የመያዝ አቅም በላይ ማስተናገድ፤

፬. በማንኛውም ህንፃ ውስጥ ሰዎች እያሉ የአደጋ ማምለጫዎችን መዝጋት ወይም መቆለፍ፤

፭. በእሳትና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ወቅት ለህዝብ አገልግሎት የተዘጋጁ የአደጋ ማምለጫ በሮችን ወይም የጭስ መከላከያ ክፍሎችን ወይም አውቶማቲክ የአየር መቆጣጠሪያ መግቢያዎችን መከልከል ወይም ማገድ፤

4. The matters for deliberations by the board shall be presented by the heads of the executive organs that are members of the board for implementing this Regulation;
5. The meeting agenda of the board should be received by the members three days before the meeting;
6. Notwithstanding the provisions of this Article, the board may issue its internal meeting and operational procedures.

## Part Five
## Prohibited Actions, Taking Measures, and Administrative Penalties

### 19. Prohibited Actions

1. Carry out activities that hinder the easy passage of fire accidents controlling vehicles and equipment on any roads;
2. Interfere, disrupt or prevent employees of the commission that are engaged in any disaster prevention and controlling activities from carrying out their duties properly;
3. Accommodate individuals in cinemas, theatres, stadiums, or other public gathering buildings more than the authorized capacity of the thereof;
4. Closing or locking emergency escapes in any buildings in the presence of persons;
5. Preventing or blocking emergency escape doors, or smoke proof rooms, or automatic ventilation systems that are prepared for public use during a fire and other fire and emergency disasters;

፮. ለአደጋ መቆጣጠሪያነትና ለድንገተኛ ህክምና አገልግሎት የተዘጋጀውን ማንኛውንም መሳሪያና ተሽከርካሪ ለሌላ አገልግሎት ማዋል፤

፯. ሀሰተኛ ወይም የተጭበረበረ የአደጋ ማንቂያ ደወል ማሰማት፤ ወይም ሀሰተኛ የድንገተኛ አደጋ ድረሱልኝ ጥሪ ማቅረብ ፤

፰. በተለያዩ ሥፍራዎች ላይ ለአደጋ መቆጣጠር ሥራ የሚውሉ የእሳት አደጋ መቆጣጠሪያ መሳሪያ ለብልሽት መዳረግ፣ ከቦታ ቦታ ማንቀሳቀስ፣ ወደ ግል ይዞታ ውስጥ ማስገባት፣ በላያቸው ላይ ግንባታ ማካሄድ፣ ቆሻሻ መድፋት፣ ለሌላ አገልግሎት ማዋል ወይም ከእሳት አደጋ መሳሪያ ውሃ መቅዳት፤

፱. በተቋማት ህንጻዎች ውስጣዊ ክፍሎች በሚገኝ መተላለፊያ፣ የደረጃ መወጣጫና ማለፊያ፣ ኮሪደር፣ ባልኮኒ እና ለአደጋ መከላከል የደህንት ምልክት የተደረገበትን ቦታ መዝጋት፤ መሰናክል እንዲኖር ማድረግ፤

፲. በቀላሉ ለእሳት ቃጠሎ አደጋ ሊያጋልጡ በሚችሉ ስፍራዎች እና ከፍተኛ ሙቀት ያለባቸው ቦታዎች አካባቢ ሲጋራ ማጨስ፣ እንዲሁም የተለኮሰ ሲጋራ ወይም ተቀጣጣይ ነገሮችን በየቦታው መጣል ወይም ማከማቸት፤

፲፩. በማንኛውም ህንጻና በህንፃው መዋቅር ውስጥ ስራ ማከናወኛ መሳሪያ ላይ ለቅድመ አደጋ መከላከል አገልግሎት ሲባል የተለጠፉ ምልክቶችን፣ ማህተሞችን፣ ታጎችን፣ ማስታወቂያዎችን፣ እና ሌሎች ፅሑፎችን ማንሳት፣ መቅደድ፣ ማበላሸት ወይም መሸፈን፤

6. Using any material and vehicle that are prepared for disaster controlling and emergency medical service for other services;
7. Making false or fraud emergency alarms, or making false emergency response calls;
8. Causing damage in fire accidents controlling materials that will be used for disaster control at different places, moving them from place to place, including them within once own premises, carrying out constructions on it, dumping wastes on it, using it for other purposes, or taking water from hydrants;
9. Closing of passageways, stairwells and passages, corridors, balcony, and places having disaster prevention safety signs in the interior parts of buildings of institutions;
10. Smoking around places that are vulnerable to fire accidents and high temperatures as well as throwing away or accumulating lit cigarettes or inflammable materials;
11. Removing, tearing apart, damaging, or covering signs, seals, tags, notices, or other writings that are posted on working materials in any building and its structure for pre-disaster mitigation service;

፲፪. በማንኛውም ህንጻና በህንፃው መዋቅር ውስጥ የኤሌክትሪክ ሽቦዎችን ማገናኘት ወይም መነካካት ወይም የኤሌክትሪክ ስርዓት ከተሰራበት አቅም በላይ ሃይል መጫን ወይም የኤሌክትሪክ ስርዓቱ ደህንነት ገጽታ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ድርጊት መፈጸም፤

፲፫. በሚመለከተው አካል ሳይረጋገጥ ህንፃው ወይም ግንባታው ሳይጠናቀቅ በከፊል ወይም በሙሉ ለማንኛውንም አገልግሎት ማዋል፤

፲፬. ማንኛውም የህንፃ ግንባታ በሚካሄድበት ወቅት የሠራተኛው ደህንነት መጠበቂያ መስፈርቶች ሳይሟሉ ግንባታ ማካሄድ፤

፲፭. ለአደጋ ሊያጋልጡ የሚችሉ የተቆፈሩ ጉድጓዶችን አለመከለል ወይም መክደኛ አለማድረግ፣ ለሕንጻ ግንባታ ሥራ የሚውሉ ጠንካራ ስካፎልዲንግ አለመጠቀም፣ በቀላሉ ሊደረመስ የሚችል አፈር ወይም የግንባታ ተረፈ ምርት ማከማቸት፣ ክፍት የሆኑ የፍሳሽ ማስተላለፊያ ቦዮችን የአደጋ መከላከያ ምልክት አለማድረግ፤

፲፮. ይህን ደንብ የሚጻረሩ ሌሎች ተግባራትን መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡

## ፳. ስለእርምጃ አወሳሰድ

፩. ኮሚሽኑ በማንኛውም ተቋም ላይ በየጊዜው ፍተሻዎችን በማካሄድ የተሟሉና ያልተሟሉ የአደጋ ደህንነት መስፈርቶችን በመለየት ያልተሟሉ መስፈርቶች እንዲሟሉ የሙያ ምክርና የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት፣ እንዲሁም በጊዜ ገደብ በማስቀመጥ የማስተካከያ እርምጃ እንዲፈፅሙ በፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፤

12. Connecting or tampering with electric wires in any building and its structure or loading power that exceeds the installed electric system or carrying out any action that affects the safety of the electric system;
13. Utilizing a building or construction entirely or partially for any service before its completion and the verification of same by the relevant organ;
14. Carry out construction works without fulfilling safety requirements of employees during the construction of any building;
15. Not protecting or putting covers on excavated holes that could cause a disaster, not using strong scaffoldings, accumulating soils or construction by-products that could easily collapse, not putting disaster prevention signs around open sewerage lines;
16. Carrying out other activities that do not comply with this Regulation.

## 20. Taking Measures

1. The commission shall give professional consultation and technical support service for any institution to fulfill disaster safety requirements through conducting periodic inspections and identifying whether the thereof are met or not; as well as give a written warning for institutions to take remedial measures within a specified period;

፪. በተሰጠው ማስተካከያ እርምጃ መሠረት የተጓደሉ መስፈርቶች ስለመሟላታቸው ዳግም ፍተሻ በማካሄድ መስፈርቶቹ ያልተሟሉ ከሆነ ኮሚሽኑ ግለሰቡ ወይም ተቋሙ መስፈርቶችን ያላሟላ መሆኑን የሚገልፅና ቀጣይ እርምጃ እንደሚወሰድበት በድጋሚ በፅሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጣል፣ ማስጠንቀቂያውን ለሚመለከታቸው አካላት በወቅቱ ያሳውቃል፤

፫. በተሰጠው ማስጠንቀቂያ መሠረት ግለሰቡ ወይም ተቋሙ ጥፋቱን ያላስተካከለ ወይም መስፈርቶችን ያላሟላ ከሆነ የደህንነት መስፈርቶችን ባለማሟላት ምክንያት የንግድ ሥራ ፈቃዱ ወይም የስራ ፈቃዱ እንዲታገድ ኮሚሽኑ ፈቃዱን ለሰጠው አካል ያሳውቃል፤

፬. የደህንነት መስፈርቶች ሳይሟሉ እንደተሟሉ አድርጎ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሰጠ ባለሙያ ወይም የተቀበለ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ተቋም የተገኘ እንደሆነ ኮሚሽኑ የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያግዳል ወይም ይሰርዛል ወይም እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎች ይወስዳል፤

፭. የአደጋ ደህንነት መስፈርቶች ባለመሟላታቸው ወይም ለተቋሙ ደህንነት ጥንቃቄዎች ባለመደረጋቸው ምክንያት በተቋሙ ውስጥ አደጋ ቢከሰትና በተቋሙ ማህበረሰብ እና ተገልጋይ ህዝብ ህይወትና ንብረት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ ማንኛውም ግለሰብ ወይም ተቋም አግባብነት ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

2. The commission shall inspect for the second time to check whether the requirements are fulfilled or not according to the provided remedial measures, and give a second written warning which states that the individual or institution did not fulfill the requirements and the taking of further measures; notify the warning to the concerned organs timely;
3. If the individual or institution does not rectify his failure or fulfill the requirements according to the provided warning, the commission shall inform the organ that issued the business license or working license to suspend it due to not fulfilling the safety requirements;
4. If there is an expert that provides or an individual or institution that receives a competency assurance certificate by faking the fulfillment of safety requirements, the commission shall suspend or revoke the competency assurance certificate or take other administrative measures as deemed necessary;
5. Any individual or institution shall be held accountable in accordance with the relevant laws if a disaster occurs in an institution by not fulfilling disaster safety requirements or failing to take precautions for the safety of the institution and as a result, the damage is inflicted on the lives and properties of the community and customers of the thereof.

## ፳፩. ስለ አስተዳደራዊ ቅጣት

፩. ማንኛውም ሰው በተቋሙ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ የአደጋ ደህንነት መስፈርቶች ሳይሟላ የቀረ እንደሆነ እንደ ደረጃው ከብር 10,000.00 (አሥር ሺህ ብር) ያላነሰና ከብር 100,000.00 (መቶ ሺህ) ያልበለጠ የገንዘብ ቅጣት ይጣልበታል፤

፪. የቅጣት ክፍያው የሚስተካከሉ ወይም መታረም ያለባቸውን ማስተካከልን አያስቀርም፤

፫. በዚህ ደንብ የሚጣለው ቅጣት ሌሎች የፍትሐብሔር ቅጣቶችን አያስቀርም፤

፬. ይህንን ደንብ በመተላለፍ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የቅጣቱ ማስታወቂያ ከተሰጠው ቀን አንስቶ በ፲፭ የስራ ቀናት ውስጥ ኮሚሽኑ ዘንድ በመቅረብ ቅጣቱን ገቢ ማድረግ አለበት፤

፭. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) የጥፋት ደረጃዎች ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ስድስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፳፪. ስለ ቅሬታ አቀራረብ ስርዓት

ኮሚሽኑ፡-

፩. የአደጋ ስጋት ደህንነት አቤቱታና ቅሬታ እንዲሁም የአፈጻጸም ሁኔታ የሚከታተል የቅሬታ ሰሚና አፈታት ኮሚቴ ያደራጃል ፤ የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት እና ዝርዝር አፈጻጸም በመመሪያ ይወሰናል፤

፪. ኮሚቴው የቀረበውን አቤቱታ ከዚህ ደንብና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር አገናዝቦ በመመርመር በቀረበው አቤቱታ ላይ በ፴ ቀናት ውሳኔ ይሰጣል፤

## 21. Administrative Measures

1. If an individual fails to fulfill the necessary disaster safety requirements in an institution, a penalty of birr 10,000.00 (ten thousand birr) and not more than birr 100,000.00 (one hundred thousand birr) shall be levied on him according to the set forth categories;
2. The penalty payment shall not exculpate those matters that should be rectified or corrected;
3. The penalty imposed by this Regulation shall not exclude other civil law-related penalties;
4. Any person that violated this Regulation and penalized should pay the penalty for the commission within 15 working days of receiving the notice;
5. The offense categories indicated under Sub-Article (1) of this Article shall be specified through a directive to be issued by the commission.

## Part Six
## Miscellaneous Provisions

## 22. Complaint Submittal Procedure

The commission shall:-

1. establish a complaint hearing and resolution committee that follows up disaster risk safety complaints and grievances as well as the execution of the thereof; the duties and responsibilities and specific implementation procedures shall be specified through a directive;
2. the committee shall examine the submitted complaint with respect to this Regulation and other relevant laws and make a decision within 30 days;

፫. አቤቱታው ተመርምሮ የተከፈለው ቅጣት አላግባብ መሆኑ ሲረጋገጥ በከተማ አስተዳደሩ ፋይናንስ ሥርዓት መሠረት ቅጣት የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ይሆናል፤

፬. የኮሚሽኑ የቅሬታ ሰሚና አፈታት ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፴ ቀናት ውስጥ ለኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፤

፭. የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊ ቅሬታ በቀረበ በ፲ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፤

፮. የኮሚሽኑ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን አግባብ ላለው የአስፈጻሚ አካል ወይም ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

**፳፫. መረጃ ስለመስጠትና ማቅረብ**

የአደጋ ደህንነት መስፈርቶችን አሟልቶና ጠብቆ ሥራውን ማከናወን ያለበት ማንኛውም ሰው የሚጠየቁ ማናቸውንም ከአደጋ ደህንነት መስፈርቶች ጋር የተያያዙ መረጃዎች የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**፳፬. ስለመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**፳፭. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ኮሚሽኑ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

3. if the complaint is examined and it is confirmed that the penalty was paid inappropriately, the payment shall be refunded as per the finance procedure of the city government;
4. an individual who is not satisfied with the decision given by the complaint hearing and resolution committee of the commission could submit his complaint to the head of the commission within 30 days of receiving the decision;
5. the head of the commission shall give his decision within 10 days of the submittal of the complaint;
6. an individual who is not satisfied with the decision of the head of the commission could submit his complaint to the relevant executive organ or a competent court.

**23. Provision and Submittal of Information**

Any individual who must fulfill and maintain disaster safety requirements and carry out his activities is obliged to provide any information which is related to disaster safety requirements.

**24. Duty to Cooperate**

Any person shall be duty-bound for the implementation of this Regulation.

**25. Power to Issue Directives**

The commission may issue directives that are necessary for the implementation of this Regulation.

**፳፮. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም የከተማው ካቢኔ ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

**፳፯. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከ ሰኔ ፮ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ ፮ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም**

**አዳነች አቤቤ**

**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

**26. Inapplicable Laws**

Any Regulation or directive or customary practices of the cabinet which are inconsistent with this Regulation shall have no effect.

**27. Effective Date**

This Regulation shall enter into force as of this 13th day of June 2022.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of June 2022.**

**Adanech Abiebie**
**Mayor of Addis Ababa City**